የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 3 እና 4

1. ስለ መጥምቁ ዮሐንስ “ የእግዚአብሔርን መንገድ አዘጋጁ፤ ጥርጊያውንም አስተካክሉ እያለ በምድረ በዳ የሚያስተምር የዐዋጅ ነጋሪ ቃል” ብሎ ትንቢት የተናገረው ነቢይ ማን ነው?
ሀ) ኢሳይያስ ለ) ኤርምያስ ሐ) ሆሴዕ መ)ሕዝቅኤል

2. "እነሆ፥ ሰማይም ተከፈተ የእግዚአብሔርም መንፈስ በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥ አየ። እነሆም፥ 'በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው' የሚል ድምጽ ከሰማይ መጣ" የሚለው የትኛውን ምሥጢር የሚገልጥ ነው?
ሀ) ምሥጢረ ጥምቀት ለ) ምሥጢረ ስጋዌ ሐ) ምሥጢረ ሥላሴ መ) ምሥጢረ ትንሳኤ ሙታን

3. መጥምቁ ዮሐንስ ወደ እርሱ መጥተው ታጢአታቸውን የሚናዘዙ ሰዎችን የሚያጠምቃቸው በየት ነበር?
ሀ) ዮርዳኖስ ወንዝ ለ) ገሊላ ባሕር ሐ) ሰሊሖም መጠመቂያ መ) ቀይ ባሕር

4. ዮሐንስም ለሕዝቡ "እኔ ለንስሓ በውሃ አጠምቃችኋለኹ፤ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል እርሱ በ_____ ያጠምቃችኋል" አላቸው
ሀ) መንፈስ ቅዱስ ለ) ነፋስ ሐ) እሳት መ) ውሃ ሠ) ሀ እና ሐ ረ) ሁሉም

5. መጥምቁ ዮሐንስ "እናንተ የእፉኝት ልጆች፥ከሚመጣው ቁጣ እንድትሸሹ ማን አመለከታችኹ? እንግዲህ ለንስሓ የሚገባ ፍሬ አድርጉ" ብሎ የተናገረው ለማን ነው?
ሀ) ቀራጮች ለ) ጭፍሮች ሐ) ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን መ) ለመማር የተሰበሰበውን ሕዝብ

6. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መረባቸውን ወደ ባሕር ሲጥሉ አይቶ “ኑ ተከተሉኝ፤ ሰውን የምታጠምዱ እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ” ብሎ የጠራው እነማንን ነው?
ሀ) ስምዖንንና ወንድሙን እንድርያስን ለ) ያዕቆብንና ወንድሙን ዮሐንስን
ሐ) ፊልጶስንና ናትናኤልን መ) ያዕቆብንና ይሁዳን

7. ጌታን የተከተሉት ሁለቱ የዘብዴዎስ ልጆች እነማን ናቸው?
ሀ) ስምዖን እና እንድርያስ ለ) ያዕቆብ እና ዮሐንስ ሐ) ዮሐንስ እና እንድርያስ መ) ያዕቆብ እና ይሁዳ

8. ዲያብሎስ ጌታችንን ስንት ጊዜ ፈተነው?
ሀ) አንድ ጊዜ ለ) ሦስት ጊዜ ሐ) ሁለት ጊዜ መ) በጭራሽ አልፈተነውም

9. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ ወደ ምድረ በዳ ወጥቶ ለ _____ ጾመ።
ሀ) አርባ ቀን ለ) አርባ ሌሊት ሐ) ሠላሳ ቀን መ) ሠላሳ ሌሊት ሠ) ሀ እና ለ ረ) ሐ እና መ

10. ከሚከተሉት ውስጥ ዲያብሎስ ለጌታችን ካቀረባቸው ፈተናዎች ውስጥ ይካተታል?
ሀ) የዓለምንም መንግሥታት ሹሉ ከብራቸውንም አሳይቶ"ወድቀኽ ብትሰግድልኝ ይህን ሹሉ እሰጥኻለኹ" አለው።
ለ) "የእግዚአብሔር ልጅ ከኾንኽ፥ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲኾኑ በል" አለው።
ሐ) "መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልኻል እግርኽንም በድንጋይ ከቶ እንዳትሰናከል በእጃቸው ያነሡኻል ተብሎ ተጽፏልና፥ የእግዚአብሔር ልጅስ ከኾንኽ፥ወደ ታች ራስኽን ወርውር" አለው
መ) ሁሉም መልስ ናቸው

11. ዮሐንስ መያዙን ከሰማ በኋላ ጌታችን በየት መኖር ጀመረ?
ሀ) ቅፍርናሆም ለ) ናዝሬት ሐ) ደብረዘይት መ) ደብረ ታቦር

12. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ ለመጾም ወደየት ሄደ?
ሀ) ቅፍርናሆም ለ) ደብረዘይት ሐ) ገሊላ መ) ገዳመ ቆሮንቶስ

13. መጥምቁ ዮሐንስ ልብሱ የግመል ጠጉር ነበር፣ በወገቡም የጠፍር መታጠቂያ ነበር፤ ምግቡም _____ ነበር።
ሀ) የበረሐ እንስሳት ለ) አንበጣ ሐ) የጣዝማ ማር መ) ለ እና ሐ ሠ) መልስ የለም

14. ለተጠሩት ሐዋርያት የተገባላቸው ቃል ምን ነበር?
ሀ) በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ
ለ) የመንግስተ ሰማያት መክፈቻ እሰጣችሁ ዘንድ በኋላዬ ኑ
ሐ) የሕይወትን እንጀራ ትበሉ ዘንድ በኋላዬ ኑ
መ) ሁሉም መልስ ነው

15. በማቴዎስ ምዕራፍ 4 ላይ የተጠሩት ሐዋርያት ከምን ስራ ተጠሩ?
ሀ)ከቀራጭነት ለ)ከአሳ አጥማጅነት ሐ)ከግብርና መ) ከውትድርና

16. ጌታችን ሲጠመቅ የእግዚአብሔር መንፈስ በምን አምሳል ወረደ?
ሀ) በእሳት ለ) በቁራ ሐ) በርግብ መ) በብርሃን

17. መጥምቁ ዮሐንስ “መንሹም በእጁ ነው፥ አውድማውንም ፈጽሞ ያጠራል፥ ስንዴውንም በጎተራው ይከታል፥ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል” ብሎ የተናገረው ስለማን ነው?
ሀ) ስለ እራሱ ለ) ስለ ኤርሚያስ ሐ) ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መ) ስለ ሁሉም

18. ጌታችን ከሚከተሉት ከተማዎች ውስጥ ማስተማር የጀመረው በየት ነው?
ሀ)ዛብሎን ለ) ንፍታሌም ሐ) ናዝሬት መ) ሀ እና ለ

19. ከሚከተሉት አንዱ ምዕራፍ 4 ላይ ጌታችን ከጠራቸው ውስጥ አይመደብም?
ሀ)ጴጥሮስ ለ)እንድርያስ ሐ)ያዕቆብ መ)ቶማስ ሠ) ሁሉም

20. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቱን ምን በማለት ጀመረ?
ሀ) እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ
ለ) ሽክማችሁ የከበደ ወደ እኔ ኑ
ሐ) በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው
መ) መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ

21. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማን እጅ ተጠመቀ?
ሀ) ፊሊጶስ ለ) ጴጥሮስ ሐ)መጥመቁ ዮሐንስ መ)የዘብዴዎስ ልጅ ዮሐንስ

22. "መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል እግርህንም በድንጋይ ከቶ እንዳትሰናከል በእጃቸው ያነሡሃል፡ ተብሎ ተጽፎአልና የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ፥ ወደ ታች ራስህን ወርውር፡ አለው" የሚለው ቃል ከወንጌላት ሌላ የት ይገኛል?
ሀ) ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 22
ለ) ኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ 8
ሐ) ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ ፲፩
መ) መዝሙር 90